# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፩፣ ቁጥር ፭፣ ጥቅምት ፳፻፲፬ ዓ.ም

**ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ** በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት።




"የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የመቋቋም አቅም ማሳደግ ለተባበሩት መንግስታት ዘላቂ የልማት ግቦች ስኬት አስተዋጽኦ ያደርጋል"

የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፐ/ር ፈቃዱ በየነ

## በዚህ እትም. . .

REDD+ ፕሮግራም በኢትዮጵያ፤ ዕቅድና ስኬት ፪

ዜናዎች ፪

ሁነቶች ፯

የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች ልማትና ሽግግር በኢትዮጵያ ፯

ልዩ ልዩ ህትመቶች ፰



**ዋና አዘጋጅ፡** ንጉሱ ለማ ገብሬ

**አዘጋጆች፡** ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ እና ሮቢ ረዳ

**አምደኞች፡** መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡** አርሴማ አንዳርጋቸው

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭

## ዜናዎች

### አየር ንብረት ለውጥን የተመለከተ ቀጠናዊ ምክክር ተካሄደ

የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና የልማት ትብብር ድርጅት ከቀጠናው ሀገራት ከተውጣጡ ባለሞያዎች ጋር በአዲስ አበባ የአየር ንብረት ለውጥ እርምጃዎች በሚመለከቱ "መረጃዎች እና መሣሪያዎች" ላይ ከመስከረም 3 እስከ 7 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ምክክር አካሂዷል።

ስብሰባውን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ የአካባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፕ/ር ፈቃዱ በየነ በንግግራቸው "የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የመቋቋም አቅም ማሳደግ ለተባበሩት መንግስታት ዘላቂ የልማት ግቦች ስኬት አስተዋጽኦ ያደርጋል" ብለዋል።

የምክክር መድረኩ የተዘጋጀበት ዓላማም የአየር ንብረት ለውጥን ማጣጣሚያና ማስተሰርያ እርምጃዎችን በተመለከተ ቀጠናዊና ሀገራዊ መረጃዎችን ለማመንጨት እና ለሌሎች ለማጋራት የሚረዱ መሳሪያዎችን ለማልማት እና ለማስተዋወቅ ታቅዶ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በምክክሩ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተገናኙ ትምህርቶች፣ የምርምርና ፈጠራ አገልግሎቶችን ለአባል አገራት ለማቅረብ ይቻል ዘንድ ከቀጠናዊ ተቋሙ የአየር ንብረት ትንበያና ትግበራ ማዕከል ጋር የመግባቢያ ሰነድ ለመፈራረም ውይይት መጀመሩ ተገልጿል።

### በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ዝቅተኛ የልቀት ልማት ስትራቴጂ ላይ የቴክኒክ ስልጠና ተሰጠ

የፓሪስ ስምምነት የተመድ የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነትን የተቀበሉ አባል ሀገራት ዓለምአቀፍ አማካይ የሙቀት መጠን ጭማሪን ከ 2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች ለመገደብ እና እንዲሁም ወደ 1.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ለመጨመር የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ይቻል ዘንድ አባል ሀገራቱ ቃል ኪዳኖቻቸውን ለማሳካት የሚረዳቸውን "የረጅም ጊዜ-ዝቅተኛ ልቀቶች ልማት ስትራቴጂያቸውን እ.አ.አ. እስከ 2020 ለሴክሬተርያቱ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል።

በዚሁ ስምምነት መነሻነት የኢትዮጵያ መንግሥት እቅዱን ለማዘጋጀትና ቁርጠኝነቱንም በተግባር ለመተርጎም ይቻል ዘንድ የጉዳዩ መሪ ተቋም በሆነው በአከባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፣ ስራውን በሚያስተገብረው የአለም አረንጓዴ ልማት ኢንስቲትዩት እና ስራውን በገንዘብ በደገፈው የፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል በመጋቢት 2013 ዓ.ም የስምምነት ሰነድ ተፈርሟል።

ይህንኑ ተከትሎ በነሐሴ 2013 ዓ.ም ኮሚሽኑ ከዓለም የአረንጓዴ ልማት ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ከኮሚሽኑና ከዘርፍ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ለተውጣጡ ባለሞያዎች የክህሎት ማሳደጊያ ሥልጠና ሰጥቷል። በሥልጠናውም የስትራቴጂው ዝግጅት የታለመለትን ግብ ለማሳካት ያስችል ዘንድ በነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና፣ በቁልፍ የፖሊሲ ዓላማዎች፣ በመረጃ ነክ መስፈርቶች፣ በዘርፍ መ/ቤቶች የነባራዊ እውነታዎች ትንተና እና ከወዲሁ ሊወሰዱ በሚኖርባቸው እርምጃዎች ላይ ውይይት ተካሄደ ል።

### REDD+ ፕሮግራም በኢትዮጵያ፤ ዕቅድና ስኬት

- ዶ/ር ይተብቱ ሞገስ፣ በየአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የREDD+ ሴክሬታሪየት ብሄራዊ አስተባባሪ

**መግቢያ**

REDD+ ከደን መጨፍጨፍ፣ መመናመንና የሚለቀቀውን ልቀት ለመቀነስ፣ ደንን በዘላቂነት ለመጠቀምና ለመጠበቅ፤ በታዳጊ ሀገራት የካርቦን ክምችትን ለመጨመር የሚጠቅሙ ተግባራት ዙሪያ መመሪያ ለመስጠት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ማዕቀፍ (UNFCCC) የተፈጠረ ማዕቀፍ ነው። ግንባር ቀደም ዒላማውም ሀገራት በሃገር አቀፍ ደረጃ ልቀት የሚያስከትሉን የሰዎች የደን ላይ ጫናዎችን ለመቀነስ የሚከናወኑ ተግባራትን ለማበረታታት ሲሆን በጊዜያዊነት ግን በታችኛው አስተዳደር እርከን የሚከናወኑ ተግባራትንም እውቅና ይሰጣል። የREDD+ ትግበራ በሀገራት ፈቃደኝነትና የሀገራቱ ሁኔታ፣ አቅምና በሚያገኙት ድጋፍ ላይ የተመሰረተ ነው።

ማዕቀፉ በ2005 ዓ.ም በዋርሶ በፀደቀውና ለREDD+ ትግበራ የተሟላ ዘዴና የፋይናንስ መመሪያ በሚያቀርበው የዋርሶ የREDD+ ማዕቀፍ (WFR) ተብሎ ይጠራል። REDD+ በፓሪስ ስምምነት አንቀፅ አምስት ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ሲሆን አባል ሀገራት ለREDD+ ትግበራ ያላቸውን ፍላጎትና የፓሪስ ስምምነት አንደኛው አካል እንዲሆን የገለፁበት ነው። ስለዚህም WFR አባል ሀገራት በደኑ ዘርፍ ለአየር ንብረት ለውጥ ትግበራ ከፍተኛ ቁርጠኝነት ያሳዩበት መሰረት ነው።

**የREDD+ የትግበራ ምዕራፎች**

አባል ሀገራት REDD+ ፕሮግራምን የሚከተሉትን ጉዳዮች በመያዝ መተግበር እንዳለበት የተስማሙ ሲሆን እነዚህም፤

- ሀገራዊ ስትራቴጂዎች ወይንም የድርጊት መርሀ-ግብርና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ መጀመር (የዝግጅት ምዕራፍ)

ወደ ገፅ ፫

**ከገፅ ፪ የቀጠለ**

- በመቀጠል እነዚህን የተቀረፁ ፖሊሲዎችና ሀገራዊ ስትራቴጂዎች ወይንም የድርጊት መርሀ-ግብርን መተግበር ሲሆን፤ ይህም ተጨማሪ የአቅም ግንባታ፣ የቴክኖሎጂና ውጤት ተኮር የሰርቶ ማሳያ ተግባራትን ያጠቃልላል (የትግበራ ምዕራፍ)
- በመጨረሻም ወደ ውጤት ተኮር ትግበራ መሸጋገር ሲሆን፣ ይህም ሙሉ በሙሉ የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ ስርዐት ያለውና ሀገራት ውጤታማ ተግባራትን ለማከናወን የሚያግዛቸውን ሀብት የሚያፈላልጉበትና የሚያገኙበት ደረጃ ነው (ውጤትን መሰረት ያደረገ የክፍያ ምዕራፍ)

ሀገራዊ የREDD+ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽን ለማሳካት ኢትዮጵያ በአለም ባንክ የደን ካርቦን አጋርነት ፋሲሊቲ ቴክኒካልና የገንዘብ ድጋፍ በREDD+ ትግበራ ላይ ስትካፈል ቆይታለች። ሀገራዊ የREDD+ ፕሮግራምን የሚያስተባብረው ተጠሪነቱ ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የሆነው ብሄራዊ የREDD+ ሴክሬታሪያት ነው። የመጀመሪያው የዝግጅት ምዕራፍ የፕሮገራም ሰነድ የተዘጋጀው በ2003 ዓ.ም ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ ሂደት ሲሆን ፕሮግራሙ ከ 2005 እስከ 2009 ዓ.ም ሲተግበር ቆይልቷ። ኢትዮጵያ ወደ የትግበራው ምዕራፍ በ 2009 ዓ.ም የገባች ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ሁለት ሰፋፊ የ REDD+ ፕሮግራሞች በሂደት ላይ ይገኛሉ።

**የኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅድ እና REDD+**

የኢትዮጵያ መንግስት የግብርናና የገጠር መሬት አስተዳደርን ለሀገሪቱ የኢንቨስትመንት፣ የኢኮኖሚ ልማትና ድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ላለው አስፈላጊነት ትኩረት ሰጥቷል፡ ይህም በከፍተኛ ደረጃ የገጠር መሬት ገፅታ ከምግብ ዋስትና፣ ኢነርጂ ማመንጨት፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የብዝሀ-ህይወት ጥበቃ፣ የስነ-ምህዳር አስተዳደርና ከአየር ንብረት ለውጥ ችግሮች ጋር ትስስር እንዳለው እውቅና በመስጠት ነው። በኢትዮጵያ ባለፉት አስርት አመታት ሲተገበር የነበረው ዘላቂ ያልሆነው የመሬት አጠቃቀም ስርዐት በአንድ ወቅት ለምለም የነበረውን የሀገሪቱን ክፍል ወደ ደረቅ መሬትነት ለውጦታል። በአሁን ወቅት አብዛኛው የደን የመሬት ክፍል የሚገኘው በደቡብ ምዕራብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ነው። ይህም የመሬት ክፍል ለማህበረሰቡ መሰረታዊ ፍላጎቶችና አገልግሎት የሚሰጥ ስነ-ምህዳርን የያዘ ሲሆን፤ ይህም የግብርና ምርት ማሻሻልን፣ የውሀን መጠንና ጥራት መጨመርን፣ ለብዝሀ-ህይወት መኖሪያነትንና ለአየር ንብረት ቅነሳ የሚኖረውን አስተዋፅኦን ያጠቃልላል። የREDD+ ፕሮግራም የተቀረፀው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተውን የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ዒላማን ለማሳካት ብቻ ሳይሆን ለገጠሩ ማህበረሰብ ደህንነት፣ ስነ-ምህዳር ጥበቃና የሀገሪቱን የውሀ ሀብት ለማሳደግ ጭምር ነው።

በአሁን ወቅት በሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተውን የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የተካተተው የREDD+ ፕሮግራም፤ ያለውን የተፈጥሮ ደን በተሻሻለ መንገድ በማስተዳደር እና ደንን በማስፋፋት ወይም መልሶ በማልማት የደን ሽፋንን በመጨመር የCRGE/NDC ዒላማዎችን ለማሳካት አስተዋፅኦ ያደርጋል። በተከለሰው ሀገራዊ የደን መረጃ መሰረት 15.5% የሀገሪቱን ሽፋን የሚይዘው 17.2 ሚሊዮን ሄክታር ደን፣ በየአመቱ 0.54% በሆነ መጠን የደን መጨፍጨፍ አደጋ እየገጠመው ይገኛል (Ethiopia's FREL, 2017)። ኢትዮጵያ እየተከሰተ ባለው የተጨፈጨፈ ደን መሬት፣ የተመናመነ ደን መሬት ምክንያት ደንን በመጠበቅና መልሶ በማልማት የሙቀት አማቂ ጋዝን ለመቀነስ፣ ካርቦንዳይ ኦክሳይድን ለማግለልና ለአየር ንብረት ለውጥ አልበገሬነትን ለመጨመር ከፍተኛ አቅም አላት።

በተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተው የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ላይ ከመሬት አጠቃቀም ለውጥና ከደን ልማት ዘርፍ ከፍተኛ የስርየት አቅም እንዳለ ተቀምጧል። በተመሳሳይ መንገድም ዘርፉ በተለመደው ኳላቀር አሰራር ቢቀጥል ከእንሰሳት ሀብት በመከተል ከፍተኛ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ይኖረዋል። በመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ልማት ዘርፍ የሚተገበሩ የፖሊሲ ተግባራት በ2022 ዓ.ም የሚኖረውን የልቀት መጠን ወደ -99.9 ሚ.ሜ.ቶን ካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ እንዲወርድ ማድረግ የሚችል ሲሆን ይህም አጠቃላይ ዘርፉን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ያደርጋል። REDD+ ከመሬት አጠቃቀም ለውጥና ከደን ልማት ዘርፍ የሚኖረውን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ታስቦ የተቀረፀ ፕሮግራም ነው።

ከመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ልማት ዘርፍ የሚኖረው የተጣራ የልቀት ቅነሳ ሊሳካ የሚችለው የደን ጭፍጨፋንና መመናመንን በመቀነስ፣ በቦን ቻሌንጅና ኒውዮርክ ሰሚት ቃል በተገባው መሰረት ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ደንን መልሶ በማልማትና 15 ሚሊዮን የሚሆነውን መሬት በደን በመሸፈን ነው። የኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተው የአየር

**ወደ ገፅ ፬**

**ከገፅ ፫ የቀጠለ**

ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ውስጥ የተቀመጠው የደን መልሶ ማልማት ዒላማ  በሁለት የሚከፈል ሲሆን የመጀመሪያው 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ዛፍ በመትከል ሲሆን ሌላው ከ5 - 6 ሚሊዮን ሄክታር የተፈጥሮ ደንን መልሶ እንዲያገግም በማድረግ ነው። ይህም በደን ዘርፍ የልማት ዕቅድ መሰረት የደኑ ዘርፍ የረጅም ዘመን ዕቅድ ግብ ሁኖ ቆይቷል። ይህንን የላቀ ዕቅድ ማሳካት የደን ሽፋንን ወደ 30% የሚያሳድገው ሲሆን ይህም በርካታ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

**የREDD+ ትግበራ ደረጃ**

በአሁን ወቅት በትግበራ ላይ ያሉ ሁለት ዋና ዋና የREDD+ ፕሮግራሞች አሉ። ፕሮግራሞቹ በአለም ባንክ BioCF እና በኖርዎይ መንግስት የአለም አቀፍ የደንና አየር ንብረት ትግበራ (NICFI) የሚደገፉ ሲሆን፣ ከፍተኛ አቅም ያላቸውን 5 ክልሎች ያጠቃልላል።ፕሮግራሞቹም፤

1. የኦሮሚያ የደን መልክዓ ምድር ፕሮግራም (OFLP) እና
2. የREDD+ ኢንቬስትመንት ፕሮግራም (RIP) ናቸው።

***1. የኦሮሚያ የደን መልክዓ ምድር ፕሮግራም (OFLP)***

የኦሮሚያ የደን መልክዓ ምድር ፕሮግራም (OFLP) የተቀረፀው ከBioCF ተጨማሪ የኢንቨስትመንት እርዳታዎችን ለመሳብ፣ የተሻሻለ ከመሬት አጠቃቀም የሚገኝ አሻራን ለማምጣት፣ ደንን ለማቆየትና ከዚህ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ ነው። ከለጋሽ አካላት የተገኘው መነሻ የ18 ሚሊዮን ብር የኢንቨስትመንት ካፒታል ከልቀት ቅነሳ የሚገኝ ክፍያ ለማግኘት የሚከናወኑ ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እና ትግበራንና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ጥቅም ላይ ውሏል። ስለዚህ OFLP ትግበራን ለማስፋፋት አቅም ሆኗል። ፕሮግራሙ ከባዮ-ካርቦን ፈንድ እስከ 50 ሚሊዮን ብር ለሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ቅነሳ የሚከፈል ውል ውስጥ ለመግባት የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ተደርገውበታል፣ ይህም ስምምነት ላይ በተደረሰበት የመነሻ መጠን ላይ ተመርኩዞ እስከ አስር ዓመት [2013-2022] ተፈጻሚ የሚሆን ነው።

የOFLP የከፍተኛ ደረጃ የውጤት አመላካቾች፤ የኦሮሚያ ክልልን እንደ አንድ የልኬት ቦታ በመውሰድ የ10 ሚ.ሜ.ቶን ልቀት ቅነሳን እና የ71,056 ሄክታር ደን መጨፍጨፍን መቀነስን ያጠቃልላል። ዝቅተኛ ደረጃ ውጤቶች ደግሞ ሀ) 12,000 ሄክታር የደን ቦታን በደን አስተዳደር ዕቅድ ማካተትን  ለ) 9,000 ሄክታር መሬትን መልሶ ማልማትን ሐ) 30%ቱ ሴቶች የሆኑበትን 25,000 ግለሰቦች ተጠቃሚ ማድረግ ያጠቃልላል።

ከፍተኛ ውጤት በOFLP ትግበራ የተመዘገበ ሲሆን ከአለም ባንክ ጋር የልቀት ቅነሳ ክፍያ ስምምነት (ERPA) ለማድረግ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

***2. የREDD+ ኢንቬስትመንት ፕሮግራም (RIP)***

በአረንጓዴ ስትራቴጂ ላይ የተቀመጠውን የላቀ ዕቅድ ለማሳካት በኢትዮጵያና በኖርዌይ መንግስታት መካከል ለአራት አመታት የሚቆይ የ600 ሚሊዮን ኖክ ማለትም ወደ 75,000,000 ዶላር የሚጠጋ የትብብር ስምምነት በሀምሌ 2010 ዓ.ም  ተፈርሟል። ፕሮግራሙ በአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፣ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በአምስት ክልሎች (አማራ፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ እና ትግራይ) የጋራ ትብብር እየተተገበረ ሲገኝ ውጤት ላይ ያተኮሩ ተግባራትን በማከናወን የደን የመመናመንና የመጨፍጨፍ መንስኤዎችን ለመቅረፍ ያለመ ነው። ይህም የአቅም ግንባታንና ፈጠራን ሲያጠቃልል ከዚህም በተጨማሪ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ፣ የህጎችን ተተግባሪነት የሚያረጋግጡና ባለው መዋቅር ለመተግበር የሚያስችሉ የፖሊሲ መሳሪያዎችን ጥቅም ላይ አውሏል።

RIP ሶስት ተጓዳኝ ምሰሶዎች ያሉት ሲሆን እነዚህም

1. ማህበረሰብ ተኮር የደን ልማትና መልሶ ማልማት (AR/ANR).
2. በደቡብ ምዕራብ ክፍል የደን መጨፍጨፍና መመናመንን ማስወገድና
3. የደን ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ማስተባበሪያ ክፍል ናቸው።

***1. ማህበረሰብ ተኮር የደን ልማትና መልሶ ማልማት እና ተፈጥሮ በራሱ እንዲያገግም መርዳት (AR/ANR)***

የኢትዮጵያ የመሬት ገፅታ በከፍተኛ ደረጃ የተመናመነ ሲሆን ይህንንም ለመቅረፍ እንክብካቤ ማድረግ ያስፈልጋል። ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ስልታዊ የደን ልማትና መልሶ ማልማት አለማካሄድ የተቀረውን ብዝሀ-ህይወትና የካርቦን ክምችት ያለበት የደን ቦታ እንዲጠፋ ያደርገዋል። ይህም ማለት ARና ANR የደን ሽፋን እንዲጨምር ከማድረጋቸው በተጨማሪ የተመናመኑ ቦታዎች እንዳይስፋፉ፣ የስነ-ምህዳር ምርታማነትና ዝቅተኛ ኑሮ ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍል አኗኗርን ለማሻሻል እና ከዚህ በተጨማሪ በሀገሪቱ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የደን ክፍሎች ለመጠበቅ ይረዳል። በዚህም መሰረት RIP በአምስቱ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ 54 ወረዳዎች 54,000 ሄ/ር እና 729,000 ሄ/ር የተመናመነን መሬት AR እና ANRን፣ በቅደም ተከተል በመጠቀም በደን ልማትና መልሶ ማልማት ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ አቅዷል። እስከ በጀት አመቱ መጨረሻ ድረስ

**ወደ ገፅ ፭**

**ከገፅ ፬ የቀጠለ**

35,749.13 ሄ/ር (የዕቅዱ 66.2%) አዲስ የማህበረሰብ የደን መሬት-ገፅታ በAR ተፈጥሯል፡፡ በተመሳሳይም 715,841.34 ሄ/ር (98.2%) የተመናመነ የደን መሬት ክፍል በክለላ የማበልፀግ ዕቅድ ተዘጋጅቶለታል፡፡ ከላይ የተቀመጡት አሀዞች በአሁን ወቅት በክልሉ ባለው ግጭት ምክንያት የትግራይ ክልል ሪፖርትን አላጠቃለለም፡፡ በተጨማሪም 7,728 ሄ/ር የደን መሬት ለአሳታፊ የደን አስተዳደር (PFM) ትግበራ ተከልሏል፡፡.

## 2. የደን መጨፍጨፍንና መመናመንን መቀነስ (DD)

የDD ዋነኛ ተግባሩ ደንን በዘላቂነት ለመጠበቅ የአሳታፊ የደን አስተዳደር (PFM) አካባቢዎችን መከለልና ማህበረሰቡን ወደ ማህበረሰብ ተኮር ተቋም ማደራጀት ነው፡፡ ከታሰበው 660,00 ሄ/ር ደን 599,817.09 ሄ/ር በደቡብ፣ ኦሮሚያና ጋምቤላ የተከለለ ሲሆን ይህም አጠቃላይ ስኬቱን 90.9% አድርሶታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 263 አሳታፊ የደን አስተዳደር መሰረት ያደረጉ ማህበራትን በበጀት አመቱ መጨረሻ በኦሮሚያ፣ ደቡብና ጋምቤላ ክልል የተቋቋሙ ሲሆን ይህም ከታቀደው በ100 ብልጫ አለው፡፡ በዚህ የሪፖርት ወቅት በደቡብ ከታቀደው 147,702.37 ሄ/ር ደን 76,494.78 ሄ/ር በ5 DD ዞንና 29 DD ወረዳ ተከልሏል፡፡የተከለሉት የአሳታፊ የደን አስተዳደር ቦታዎች የአሳታፊ ደን አያያዝ ዳሰሳ ጥናት (PFRA) ያካሄዱ ሲሆን፣ የዘላቂ ደን አስተዳድር እቅድ እና የ38 አሳታፊ የደን አስተዳደር ላይ ያተኮሩ ማህበረሰብ ተኮር ድጅቶችን ህጋዊ የማድረግ ስራ እየተካሄደ ነው፡፡

በኦሮሚያ ክልል ከታቀደው 62,617.24 ሄ/ር ውስጥ 44,056.92 ሄ/ር ደን በ6 DD ዞኖችና 24 DD ወረዳዎች ለአሳታፊ የደን አስተዳደር ቦታ ተከልሏል፡፡ በዚህም ምክንያት በኦሮሚያ የአሳታፊ የደን አስተዳደር ቦታን መከለል አፈፃፀም 70.4% ደርሷል፡፡ የተከለሉት የአሳታፊ የደን አስተዳደር ቦታዎች የአሳታፊ ደን አያያዝ ዳሰሳ ጥናት (PFRA) ያካሄዱ ሲሆን፣ የዘላቂ ደን አስተዳድር እቅድ እና የ39 አሳታፊ የደን አስተዳደር ላይ ያተኮሩ ማህበረሰብ ተኮር ድጅቶችን ህጋዊ የማድረግ ስራ እየተካሄደ ነው፡፡

በጋምቤላ ክልል 54,000 ሄ/ር ደን ለመከለል ታስቦ 83,585.00 ሄ/ር (155%) በ2 ዞኖችና 6 ወረዳዎች ለመከለልና ካርታ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡ የተከለሉት የአሳታፊ የደን አስተዳደር ቦታዎች የአሳታፊ ደን አያያዝ ዳሰሳ ጥናት (PFRA) እና የዘላቂ ደን አስተዳድር እቅድ ስራ እያካሄዱ ነው፡፡ የRIP አስተዳደርን የሚያግዙ የክልል፣ ዞንና የወረዳ ሲቲሪንግ ኮሚቴና ቴክኒካል ኮሚቴ ስብሰባዎች ተካሂደዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 33,982,121 (የዕቅዱ 54%) ችግኝ ፈልቶ ለአካባቢ ጥበቃ የተከለሉ ቦታዎች ላይ ተተክሏል፡፡

## 3. የደን ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ማስተባበሪያ ክፍል (FSTU)

የደን ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ማስተባበሪያ ክፍል (FSTU) የትኩረት አቅጣጫው አዲስ ግኝትን በመጠቀም የደን ዘርፍን በተሻለ መልኩ መለወጥ እና ተጨማሪ ገንዘብ ማፈላለግ ነው፡፡ ምንም እንኳን የኮቪድ ወረርሽኝ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ለመተግበር እንቅፋት ሆኖ የቆየ ቢሆንም FSTU የታቀደው ውጤት እንዲመጣ የተቻለውን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ የተለያዩ ፅንሰ-ሀሳብ ማስታወሻዎችንና ፕሮፖዛሎችን ያዘጋጀ ሲሆን፣ ከዋነኞቹ ፕሮፖዛሎች ውስጥ 95,467,105.00 ዶላር በጀት የሚጠይቀው ከደረቃማ መሬቶች የሚኖረውን ልቀት ለመቀነስ ደንን በዘላቂነት መጠበቅ የሚለው ይገኝበታል፡፡ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ፕሮፖዛሉን ለአጋር አካላት እንዲያቀርብ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራምን ወክሎታል፡፡ ሌላ 9.8 ሚሊዮን ዶላር የሚጠይቅ ለማገዶ የሚሆን እንጨት የሚሰበስቡ ሴቶችና ህፃናት ላይ ያተኮረ የኑሮ ዘዴ ማሻሻያ ፕሮግራምም ተቀርፅዋል፡፡ FSTU 600 ሚሊዮን ክሮነር የሚጠይቀውን PRIP ክፍል II ፕሮጀክት ሰነድ ዝግጅትን በበላይነት ሲመራ የቆየ ሲሆን ይህም በኖርዌይና ኢትዮጵያ መንግስታት መካከል ያለውን ትብብር ያጠናክራል፡፡ ሌሎች የተለያዩ ፅንሰ-ሀሳብ ማስታወሻዎችንና ፕሮፖዛሎችን ተዘጋጅተው ለተለያዩ የገንዘብ ምንጮች ቀርበዋል፡፡

**ማጠቃለይ**

የብሄራዊ REDD+ ፕሮግራም የኢትዮጵያ መንግስት ዋና ፕሮግራም ተወስዶ የተመሰረተ ነው፡፡ እስካሁን የተገኘው ስኬትም ከፍተኛ ነው፡፡ ፕሮግራሙ የተቀረፀበት መንገድ ከሀገሪቱ ልቀት ከፍተኛ ድርሻውን ለመቀነስና የማጣጣሚያ ተግባራትን ለማሳለጥ የREDD+ ተግባራትን በአምስት ክልሎች ለመተግበር ነው፡፡ ከባሌ REDD+ ትግበራ የተገኘው የካርቦን ሽያጭ ገቢ ከውጤት ተኮር ትግበራ ክፍያ ማግኘት መቻልንና ህብረተሰቡ የጥረቱን ስኬት ማሳካት እንደሚችል ማሳያ ነው፡፡ REDD+ የለጋሽ ሀገራት ድጋፍና የመንግስት ቁርጠኝነት እስከ ቀጠለ ድረስ በሚቀጥሉት አመታት ውስጥ በደኑ ዘርፍ ከፍታኛው አሻራ ያሳርፋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭

## ሁነቶች

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መከሰቱንና በፍጥነት መስፋፋቱን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተካሄዱ ናቸው። የሚከተሉት በበይነ መረብ አማካይነት የሚከናወኑ ሁነቶች ለማናቸውም ታዳሚዎች ተደራሽ ናቸው። እያንዳንዱን ሁነቶች አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ‹ምንጭ› የሚለውን ማስፈንጠሪያ ይክፈቱት።

- ስርዐተ ፆታን የአየር ንብረት ለውጥ ደህንነት ማዕከል ማድረግ፣ ሲጂአይኤአር፣ ጥቅምት 2021 | ምንጭ
- በአጽኦት ማሰብ ተከታታይ ፕሮግራም፣ የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ጥቅምት 2021 | ምንጭ
- ደንና የመልክዓ ምድር መልሶ ማገገም፣ አፍሪካ ፣ ደብልዩ. አር. አይ፣ ጥቅምት 2021 | ምንጭ
- ‘የሃይድሮጂን’ ሽግግር ጉባኤ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ህዳር 2021 | ምንጭ
- የዘላቂ ፈጠራ መድረክ 2021፣ ክላይሜት አክሽን፣ ህዳር 2021 | ምንጭ
- የግብርና እና የምግብ የሽግግር ጉባኤ 2021፣ ክላይሜት አክሽን፣ ህዳር 2021 | ምንጭ
- በአፍሪካ ውስጥ ዘላቂ የእንጨት ማገዶ እሴት ሰንሰለቶች አስተዳደር፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ ምዳራዊ ልኬቶች፣ ሲፎር፣ ህዳር 2021 | ምንጭ
- ለተሻሻለ ጤናና የሰዎች አኗኗር ዘይቤ፤ ተፈጥሮንና የሰው ልጆችን መልሶ ማገናኘት፣ አይ. ሲ.ኤል.ኢ.አይ.፣ ህዳር 2021 | ምንጭ

## የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች ልማትና ሽግግር በኢትዮጵያ

❑ በየአምላክ ስራ ታመነ፤ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር ዳይሬክተር

### መግቢያ

አጀንዳ 21 በተሰኘው የሪዮ ስምምነት ላይ እንደተገለፀው "አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች" አካባቢያዊ ጠንቅ የማያስከትሉ፣ የአካባቢ ብክለታቸው አነስተኛ የሆነ፣ ሁሉንም ሀብቶች በዘላቂነት የመጠቀም ባህሪ ያላቸው፣ የምርት ተረፈ ቆሻሻዎችን እና ምርቶችን በበለጠ ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችሉና ቀሪ የምርት ውጋጆችን የበለጠ ተቀባይነት ባለው ወይም ጉዳቱን በቀነሰ መንገድ የሚያከናውኑ ቴክኖሎጂዎች ናቸው። እነዚህም የተለያዩ ንጹህ የማምረት ሂደቶችን፣ ብክለትን የሚከላከሉ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም በማምረት ሂደት ውስጥ በመጨረሻ ደረጃ የሚሰሩ ብክለትን የማስወገድ እና የመከታተል ቴክኖሎጂዎችን ያካትታሉ።

ከዚህም በላይ አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች ሸቀጦችንና የማምረቻ መሣሪያዎችን፣ የመስኖ ልማት ስርዓቶችን፣ የጎርፍ መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎችን፣ ህንፃዎችን፣ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከሮችንና የተሻሻሉ የቧንቧ መስመሮችን የውሀ ስርገትን የሚቀንሱ ቴክኖሎጂዎችን ያጠቃልላል። በተጨማሪም አካባቢ ነክ ቴክኖሎጂዎች "ሶፍት ቴክኖሎጂዎች" በመባል የሚታወቁትን እንደ ድርጅታዊና የአመራር ሂደቶች፣ ተቋማዊ አቅምን፣ በተግባራዊ ሳይንሳዊ ምርምርና በአዳዲስ የግብርና አሠራሮች ላይ የሚሰጡ የአርሶ አደሮች ትምህርት ስርአታትን እና የመሳሰሉትን ቴክኖሎጂዎችን የሚያጠቃልል ነው።

የተመድ የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ፅ/ቤት (እ.አ.አ. በ2005) ከአካባቢ ቴክኖሎጂዎች አንዱ የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ቴክኖሎጂዎችን ሲበይን “የተፈጥሮን ወይም የሰውን ስርዓት ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ወይም የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ የሚረዳ የቴክኖሎጂ አተገባበር” በማለት ይገልፃል።

### የፖሊሲ ማዕቀፎች

የአካባቢ ነክ ቴክኖሎጂዎች ሽግግርና ልማት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በአለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት ማግኘት የጀመሩት በሀገረ ብራዚል በሪዮ ዴጀኔሮ ከተማ ከተካሄደውና "የሪዮ ሰሚት" በሚባለው ጉባኤ የስምምነት አጀንዳ 21፣ እንዲሁም በተመድ የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ኮንቬንሽን አንቀፅ 4.3፣ 4.5 እና 4.7 ከተካተቱበት ጊዜ ጀምሮ ነው። እነዚህ ስምምነቶች በቀጣይ ጉዳዩን አስመልክቶ በጀርመን በርሊን በተካሄደው አንደኛው የተመድ ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (COP1) እና በአርጀንቲና በነስ አይረስ በተካሄደው 4ኛው የአባል ሀገራቱ ጉባኤ ላይ በአጀንዳነት ውይይት ተካሂዶበት የአባል ሀገራቱ ውሳኔ 2/CP4 የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋምና አሉታዊ ተፅእኖዎቹን ለመቀነስ ተስማሚ

ወደ ገፅ ፯

**ከገፅ ፮ የቀጠለ**

በሆኑና የብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ የልማት ዘርፎች ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ቁልፍ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ጉልህ ውሳኔ ተላልፏል። ከዚህም በተጨማሪ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚነት ጉዳይ በፓሪስ ስምምነት በአንቀጽ 10 ውስጥ ተካቷል። በዚሁ ስምምነት ንዑስ አንቀጽ 10.1 ላይ የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖን መቋቋምን ለማሻሻልና የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለመቀነስ የቴክኖሎጂ ልማት እና ሽግግርን አስፈላጊነት ሙሉ በሙሉ በመገንዘብ አባል ሀገራቱ በረጅም ጊዜ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ቅነሳ ራዕይን እንደሚጋሩት ያስቀምጣል። የስምምነቱ ንዑስ አንቀጽ 10.2 በተጨማሪነት “አባል ሀገራቱ በአካባቢ ቴክኖሎጂዎች ልማትና ሽግግር ላይ የትብብር እርምጃን ያጠናክራሉ” ሲል አፅንዖት ይሰጣል።

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተፅእኖ ለመቋቋም እንዲያስችላት "ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ" እ.አ.አ. በ 2011 አዘጋጅታለች። የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስልት እ.አ.አ. በ2025 የመካከለኛ ገቢ ደረጃን ለማሳካት ያለመ ነው። በተጨማሪም የልማት ስልቱ የኢኮኖሚያዊ ልማት ግቦችን በዘላቂነት ለማሳካት ለአካባቢ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን መተግበርን ታሳቢ ያደርጋል።

በርካታ ፖሊሲዎችና ዕቅዶች ግባቸውን ለማሳካት አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን እንደ አጋዥ መሣሪያ መጠቀምን ታሳቢ ተደርጎ የተቀረፁ ናቸው። እነዚህም የሀገሪቱ ህገ መንግስትን፣ የተሻሻለው ብሄራዊ የአየር ንብረት ማጣጣሚያ ዕቅድን፣ የሀገሪቱ የቀጣይ 10 ዓመት የልማት ዕቅድን፣ ሲተገበሩ የቆዩት አንደኛና ሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዶችን፣ ብሔራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድን፣ ሀገራዊ የማስተሰርያ እርምጃዎችን፣ የኢትዮጵያ የማጣጣሚያ ዕቅድ የድርጊት መርሃ ግብርን፣ የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ፕሮግራምን፣ የክልሎችና የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ስትራተጂ ፕሮግራሞችን እና የድርጊት መርሃ ግብርን ያጠቃልላሉ።

**አካባቢያዊ ተስማሚነት ያላቸውን ቴክኖሎጂዎችን የመምረጥ፣ የመሞከር፣ የመተግበር ሂደትና የተመዘገቡ ውጤቶች**

ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ውስጥ 0.04% ያህል ብቻ ታመነጫለች። ይሁንና ሀገሪቱ በአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅእኖዎች በጣም ተጎጂ ነች። የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ለአየር ንብረት ለውጥ አገራዊ ምላሽን የማስተባበር ተልእኮ ተሰጥቶታል። የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች እየጠነከሩ ሲሄዱ በሀገራችን የማጣጣሚያ እርምጃዎችን መውሰዱ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። በመሆኑም ከአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ እርምጃዎች ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችንና አግባብነት ያላቸውን መፍትሄዎችን መለየትና በአግባቡ አብራርቶ መለየት አስፈላጊ ነው። ለዚህም ስኬት "አረንጓዴ ሥራዎችን" የሚፈጥሩ መልካም ተሞክሮዎችንና የቴክኖሎጂ አማራጮችን መፈተሽ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ አማራጮችን ማየት፣ የአካባቢ መሸርሸርንና ተጋላጭነትን የሚከላከሉ እንዲሁም ተፈጥሮ በዘላቂነት ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለልማት እንድሰጥ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለይቶ መጠቀም አስፈላጊ ነው።

በአገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ተቋማትና ድርጅቶች ሲተገበሩ በነበሩ የተለያዩ አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች እና ምርጥ ልምዶች ላይ በመመርኮዝ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የሙከራ ማሳያ ፕሮጀክቶችን ሲያካሄድ ቆይቷል። ለምሳሌ ያህልም በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች አሥራ ስድስት አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች በሙከራ ሂደትና በተግባር ስራ ላይ ውለዋል። እነዚህም፤

- ከፀሐይ ኃይል የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣
- 'ከኦርጋኒክ' ደረቅ ቆሻሻ የማዳበሪያ ዝግጅት፣
- 'ከኦርጋኒክ' ደረቅ ቆሻሻ ሽክላ ማምረት፣
- በኤሌክትሪክ ሀይል የሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ የታክሲ ትራንስፖርት ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ፣
- ነዳጅ ቆጣቢ ምድጃዎችን ማምረትና መጠቀም፣
- በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ላይ የተመሰረቱ የፍራፍሬዎች፣ ሰብሎች እና ሌሎች እፅዋቶችን ማምረት፣
- የተራቆቱ የመሬት በታዎችን በመከለል መልሰ እንዲያገግሙ ማድረግ፣
- ለተጨማሪ ገቢ ማስገኛነት የሚመረቱ ዘርፈ ብዙ ዛፎችን የማልማት፣
- ከቀርከሃ የእጅ ሥራዎች ማምረት፣

**ወደ ገፅ ፰**

## ልዩ ልዩ ህትመቶች

### የአለም አቀፉ የቀዝቃዛ ምግቦች አቅርቦት ሰንሰለት ሁኔታ - አጭር መግለጫ




ይህ አጭር አፅርኦተ ዘገባ በአለም አቀፍ የቀዝቃዛ ምግቦች አቅርቦት ሰንሰለት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያሳይ ሲሆን እንደ ቴክኖሎጂዎች፣ የንድፍ አቀራረቦች፣ የፋይናንስ እና የንግድ ሞዴሎች፣ ፖሊሲ እና ዕቅድ ያሉ ሁኔታዎችን በተመረጡ ጥናቶችን ላየ ተመርኩዞ አቅርቧል። ሙሉ ዘገባው እ.አ.አ. በታህሳስ 2021 ይታተማል። ምንጭ

### የአየር ንብረት ተለዋዋጭነትና የአዝማሚያዎች ትንተና ጥናት በደቡብ ኢትዮጵያ

ይህ ጥናት የደቡብ ኢትዮጵያ ወቅታዊና ዓመታዊ የዝናብ እና የሙቀት መረጃን አዝማሚያ እና ተለዋዋጭነት ከ1983–2016 የጊዜ ገደብ ውስጥ በመውሰድና የተከታታይ ጊዜ ትንተና አሰራርን (time series analysis) በመጠቀም መርምሯል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ክልሉ ከፍተኛ የዝናብ ስርጭት ተለዋዋጭነት እንደታየበት እና ይህም በጥናቱ ወቅት የተራዘመ ድርቅና ጎርፍ እንዳስከተል አመላክቷል። ምንጭ

### ሳይንሳዊ ጥምረት 2021




ይህ ዘገባ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፅሐፊን በመወከል የዓለም ሜትሮሎጂ ድርጅት በዓለም ላይ ከሚገኙ ቁልፍ አጋር ድርጅቶችና ተቋማት ጋር በመተባበር የቅርብ ጊዜ ከአየር ንብረት ለውጥ ሳይንስ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ነባራዊ እውነታዎችን ለማቅረብ የተጠናቀረ ነው። ዘገባው ሁሉን አቀፍ ዳሰሳዎችን በማቅረብ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተዛመዱ የቅርብ ጊዜ ሳይንሳዊ መረጃዎችን እና ግኝቶችን ለፖሊሲ እና ለውሳኔ ሰጪዎች መረጃ ይሰጣል። ምንጭ

ከገፅ ፯ የቀጠለ

- የተፍጥሮ እና ቁስ-አካላዊ የአፈር እና የውሃ ጥበቃ ስራዎችን በመጠቀም የመሠረተ ልማት አውታሮችን ዕድሜ ማራዘም፣
- የኤታኖል ጋዝን ከሸንኮራ አገዳ ማምረት፣
- የወንዝ ዳርቻዎችን መልሶ በማልማት የተበከለ ውሃን ለአገልግሎት ላይ ማዋል፣
- የተፈጥሮ ማዳበሪያን ለማሳደግ እና ብክለትን ለመቀነስ ፋይዳ-ብዙ ዛፎችን መትከል ፣
- ከጃትሮፋ ተክል ፍሬዎች ነዳጅ ማምረት፣
- የስርዐተ-ምህዳር መልሶ ማገገምም፣ እና
- የኢንዱስትሪ ፍሳሽ ቆሻሻዎችን በተፈጥሮ ዘዴዎች ማከም የሚሉት ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት የቴክኖሎጂዎች እና የምርጥ ተሞክሮዎች ትግበራ በተገቢ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችና ደንቦች እንዲሁም በሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ የተደገፉ ናቸው። እነዚህ ቴክኖሎጂዎችና ምርጥ ተሞክሮዎች የአገሪቱን የተፈጥሮ ሀብቶች ዘላቂነት በማረጋገጥ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ጥቅሞችን ያረጋግጣሉ።

በተጨማሪም እንደ ንብ ማነብ፣ የዶሮ እርባታ እና እንስሳትን ማድለብ ያሉ የኑሮ ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ተካቶ በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በጋምቤላ ክልሎች ተግባራዊ ተደርጓል። ይህም በመተግበሩ በተጠቀሱት ክልሎች ብቻ 796 የአካባቢው ወጣቶች እና ሴቶች (355) አረንጓዴ የስራ ዕድል አግኝተዋል።

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እንደ ተቋም ለአየር ንብረት ቴክኖሎጂ መረብ ለተሰኘው ዓለማቀፋዊ የትብብር አውታረ መረብ ተጠሪ አካል ነው። በመሆኑም በኮሚሽኑና በዘርፍ የፌደራል ተቋማት ጥያቄ መሠረት የትስስርና ትብብር መረቡ የሚከተሉትን የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ እርምጃዎች ተግባራዊ ለማድረግ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጥቷል፤ ለኤሌክትሪክ የእንጀራ ምጣድ ደረጃ እና የአመዘጋገብ ሂደት ማውጣት፣ ለአዲስ አበባ ቀላል ባቡር የፋይናንስ ስልት ማዘጋጀት እና በኦሮሚያ፣ ደቡብ እና አፋር ክልሎች የውስጠ ምድር የሙቀት ሃይልን (ጂዎተርማል) ጥቅም ላይ ለማዋል የሚረዳ ቅድመ ጥናት ማካሄድ።

ወደ ገፅ ፱

**ከገፅ ፰ የቀጠለ**

ከነዚህም በተጨማሪ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የሙያና የገንዘብ ድጋፍ 9 ክልሎች እና 2 የከተማ አስተዳደሮች የማጣጣሚያ እና የማስተሰሪያ ቴክኖሎጂዎች የፍላጎቶች ዳሠሳ፣ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅትና የፈታኝ ሁኔታዎች ትንተና አካሂደዋል።

በተጨማሪም ለተጠቀሱት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲተገበሩ ለተለዩ የማጣጣሚያና ማስተሠርያ እርምጃዎች የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች የንድፈ ሀሳብ ሰነድ ዝግጅት ተከናውኗል። በተጨማሪም በክልሎቹና ከተማ አስተዳደሮቹ ፍላጎት ላይ በመመስረት በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ቅድሚያ የሚሰጣቸው 22 በአገር ውስጥ የሚገኙ አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች ተለይተዋል።

የክልሎችን የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች የግምገማ ሰነዶችን ዝግጅት ተከትሎ ሀገር አቀፍ የማጣጣሚያና የማስተሰሪያ ቴክኖሎጂ ፍላጎቶች የምዘና ሰነድ ተዘጋጅቶ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ስምንት (8) የማስተሠሪያ እና የማጣጣሚያ አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች ተለይተዋል። ከአምስት እስከ አሥር ዓመት የሚዘልቅ የድርጊት መርሃ ግብር፣ የፈታኝ ሁኔታዎች ትንተና እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ለሚተገበሩ ቴክኖሎጂዎች ንድፈ-ሀሳባዊ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የተለዩት አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች የሚከተሉት ናቸው:-

I. የማጣጣሚያ ቴክኖሎጂዎች

1. ከግብርና ዘርፍ (2 ቴክኖሎጂዎች)

- ጥምር ግብርና (የሰብል፣ የደንና ፍራፍሬ ምርት)
- ድርቅ እና ተባይን መቋቋም የሚችል የሰብል ዝርያዎች

2. ከውሃ ዘርፍ (2 ቴክኖሎጂዎች)

- ውሃ ማቆር
- የከርሰ ምድር ውሃ ማጎልበት

II. የማስተሰሪያ ቴክኖሎጂዎች

1. የደን ዘርፍ (2 ቴክኖሎጂዎች)

- ምርጥ ምድጃዎች
- የተለዩ ቦታዎችን በደን መሸፈን እና የተፈጥሮ የደን ቦታን መልሶ ማልማት

2. የግብርና ዘርፍ (2 ቴክኖሎጂዎች)

- እንስሳትን ማዳቀል
- የእሴት ሰንሰለት ውጤታማነት

ከላይ ከተገለፁትና እስካሁን ከተተገበሩ ቴክኖሎጂዎች በተጨማሪ በቀጣይ አስር አመታት የሚተገበረው የሀገራችን መሪ የልማት ዕቅድ 210 አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን በተለያዩ ዘርፎች ተግባራዊ ለማድረግ ያለመ ነው። የእነዚህ ቴክኖሎጂዎች ውጤታማ ትግበራ በብሔራዊ ደረጃ የኢትዮጵያን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ኢትዮጵያ የተሻሻለውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅዱን ለመተግበር ወደ 316 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልጋታል። ለአካባቢ ጥበቃ ተስማሚ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን ትግበራ የሚያራምዱ የልማት አጋሮች እና ባለድርሻ አካላት የሚያደረጉት ድጋፎች የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ዕቅድ ግቦችን ለማሳካት አስፈላጊ ናቸው።

**መደምደሚያ**

የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተፅዕኖዎች የተቀናጀ ምላሽ በሚሰጥ ሁኔታ ለመፍታት ስልት ካዘጋጁ ታዳጊ አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷና ግንባር ቀደሟ ናት። እ.አ.አ. በ2011 ተቀርጾና ተዋውቆ ሲተገበር የቆየው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስልትም የአየር ንብረት ለውጥን ተፅዖዎችን ለመቋቋምና አይበገሬነትን ለመገንባት ያለመ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ እ.አ.አ. በ2015 የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተፅእኖዎች ለመቋቋም የሚያስችል ዕቅድ አውጥታ የተገበረች ከታዳጊ ሀገሮች ቀዳሚ ሀገር ስትሆን ይህንኑ እቅድ በተሻለ መልኩ በመከለስ እ.አ.አ. በ2021 ለተመድ የአየር ንብረት ለውጥ ጽ/ቤት ካቀረቡ አገራት መካከልም አንዷ ናት።

ይሁንና በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተያያዙ በርካታ ተግዳሮቶች ያጋጥሟታል። ከነዚህም መካከል ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ፣ ከባድ እና ተደጋጋሚ ድርቅና ጎርፍ ይገኙበታል። የአየር ንብረት ለውጥን ተግዳሮቶች ለመቋቋምና ለመቅረፍ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ፍቱን መፍትሔ ሊሆን እንደሚችል ምንም ጥርጥር የለውም። በመሆኑም የሀገሪቱን የአየር ንብረት ለውጥ ስልቶችና ዕቅዶች በተገቢ ሁኔታ ለመተግበር ከአካባቢ ጋር የሚስማሙ የማጣጣሚያና የማስተሰሪያ ቴክኖሎጂዎችን ከሚፈለገው የገንዘብ እና የሙያ ሀብቶች አቅርቦት ጋር አጣጥሞ መተግበር በጣም አስፈላጊ ነው።

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዲሪ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን
ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150
ኢሜል: efcccethiopia@gmail.com
ድረ ገፅ: https://www.efccc.gov.et

## ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም። በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም።

## ስራውን የደገፉ አካላት

NDC PARTNERSHIP | IN CONTRIBUTION TO THE NDC PARTNERSHIP

Ministry of Foreign Affairs of Denmark · Federal Ministry for Economic Cooperation and Development · Supported by: Federal Ministry for the Environment, Nature Conservation and Nuclear Safety (based on a decision of the German Bundestag) · Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands · Norwegian Ministry of Climate and Environment · Norwegian Ministry of Foreign Affairs · Government Offices of Sweden, Ministry for Foreign Affairs · UK Government

Climate & Development Knowledge Network · SOUTH SOUTH NORTH — TOWARDS CLIMATE RESILIENCE

Funded by

Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands · IDRC · CRDI — International Development Research Centre / Centre de recherches pour le développement international — Canada

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.